# ሞኝ ሲናገር ፣ ብልህ ያዳምጣል

አገራችን ኢትዮጵያ ከዓለም ቀደምት የስልጣኔ ምንጭ እንደሆነች ሐገር በቀል በሆነው በግዕዝ ቋንቋ የተፃፉ ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሆኑ መዛግብት ይመሰክራሉ ። ይህንንኑ ጥንታዊ ስልጣኔዋን ከአውሮፓ ፣ ከእሲያ ፣ እንዲሁም ከመካከለኛው ምስራቅ በንግድ ፣ በጉብኝትና በዲፕሎማሲ የኢትዮጵያን አፈር ለመርገጥ ዕድሉ የገጠማቸው አብዛኛዎቹ በመጽሐፍ መልክ አሳትመው ፣ እውነታውንና ያዩትን ፣ የተገነዘቡትን ፣ በመመስከር ለታሪክ እንዲተላለፍ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክተዋል ።

ይሁንና ይህች የስልጣኔ ምንጭና የሰው ልጅ መገኛ የሆነችው ውድ ሐገርራችን ዛሬ ላይ እንዳጀማመሯ ሆና አልተገኘችም ። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ብዙ ሊያነጋግርና ብዙ ሊባልበት ስለሚችል ወደሱ ሳልገባ የቅርቡን ታሪካችንን ብቻ በመመልከትና በመመርመር እንዴት ዛሬ ካለንበት የሕብረተሰብ ዝቅጠት ደረስን? ለሚለው ጥያቄ መጠነኛ አስተያየት ለመስጠት እሞክራለሁ ። ሐገራችን ኢትዮጵያ ከሶስትና አራት ሺህ ዓመታት በላይ የዘለቀ ከወርቅ የነጠረ አኩሪ ታሪክና ዝና ቢኖራትም የቅርቡን ብቻ በመመርመር የራሴን ግንዝዛቤ አሰፍራለሁ ።

ከታሪክ እንደተማርነው በዘመናችን የተፈጠሩ አሕጉራት የሁሉም አመሰራረት ተመሳሳይ ብቻ ሳይሆን አንድ አይነት ነው ፣ ይህም ማለት አንዱ አንዱን በመውረርና ግዛቱ አንዴ ሲሰፋ አንዴ ሲጠብ አሁን ያሉበትን ቅርፅ ይዘው እናገኛቸዋለን ፣ የኢትዮጵያም አመሰራረት ከዚህ የተለየ አይደለም ። ይልቁንም ኢትዮጵያ በዓለማችን ከሚገኙት አሕጉራት ልዩ የሚያደርጋት የቅርብ ግዜ ምስረታ ያላት ሐገር ሳትሆን ለብዙ ሺህ አመታት ተከታታይነት ያለው ሉዓላዊ ሐገር እንደነበረች ታሪክ ቁልጭ አድርጎ ስለሚመሰክር ነው ። ሆኖም ግን አሁን ላለንበት ኋላ ቀርነትና ምስቅልቅል ያደረሰን የፅንፈኛ ልሂቃን እራስ ወዳድነትና የስልጣን ጥም ነው ። ይህንን ጥማቸውን ከግብ ለማድረስ ደግሞ አብዛኛው ፅንፈኞች መነሻ የሚያደርጉት ለጥቂት አመታት ተቋርጦ የነበረውን ዘውዳዊ አገዛዝ ከቁጥር ባለማስገባት ትርክታቸውን ከመሳፍንት አገዛዝና ያንን የመሳፍንት አገዛዝ አስወግዶ ወደ ቀደመው ቀጣይ ስርወ መንግሥት ከተመለሰችበትን ዘመን መሆኑ ነው ። ያንንም እንደ አዳምና ሄይዋን የፍጥረት መጀመሪያ ታሪካዊ መነሻነት በመቁጠር የሺ ዘመናት ታሪክን በመሰረዝ ፣ በማንኳሰስና ተቀባይነት እንደሌለው በማድረግ ታሪክ በማዛባት ለስልጣን ማርኪያ ሲባል ብቻ ታሪክ አልባ በሆኑና በኢትዮጵያ ታሪክና ጥንታዊ ስልጣኔ አይናቸው ደም በሚለብስ ምዕራባውያንና የአረብ ሐገሮች እገዛ እየተደረገላቸው ጭምር አዲሱን ትውልድ በፈጠራ ታሪክ አይምሮውን በመስለብ ከ40ና 50 ዓመታት በላይ ሲግቱት በመኖራቸው አዲሱ ትውልድ ታሪኩን መርምሮ እንዳያጠናና ማንነቱን እንዳያውቅ ስልታዊ ጫና በመፍጠር ፣ ግንዛቤውና ሐጉራዊ ዕውቀቱ እንዲቀጭጭና ፣ እንዲቀነጭር ከፍተኛ ስራ በመስራታቸው ዛሬ ያለንበት ፈታኝ ምዕራፍ ላይ እንድንደርስ አድርጎናል ።

የዚህ ሁሉ ማንነትን የማስካድና ፣ ማንነትን የማስረሳት ፣ ብሎም በዐይን የማይታይ በጅ የማይዳሰስ ምናባዊ ጠላት መፍጠር ፣ አያይዞም ያንን ምናብ የፈጠረውን የሕብረተሰብ ክፍል ማስረጃ በሌለው ውንጀላና ክስ በመክሰስ ፣ የፅሁፍም ይሁን የቁስ ማመሳከሪያ በሌለው አሰልቺ በሆነ ተረት ተረት ድግግሞሽ ፣ ቅኝ ሲገዛው የኖረና ለዘመናት አያት ቅድመ አያቶቹን የጨፈጨፈ አድርጎ በመሳል ፣ በሌለና ባልተፈጠረ ትርክት ቁጭትና በቀልን አርግዞ ለጥፋት እንዲነሳሳ በመቀስቀስ ፣ በተለይ በትግሬው ወያኔና በኦሮሞው ኦነጋውያን በየማሕበረሰባቸው ፣ በህፃናትና በታዳጊ ወጣቶች ዐዕምሮ ለ40 እና 50 ዓመታት መርዝን በመዝራታቸው ዛሬ ለደረስንበት ቅጥ የለሽ ስርዓትና ስጋት ዳርገውናል ።

ይህ በወያኔ ትግሬዎችና በኦሮሞ ኦነጋውያን እንደ ቅኝ ገዢና ጨፍጫፊ የተሳለው የአማራው ማሕበረሰብ ዛሬ በነዚህ ሁለት ፅንፈኞች የሞት ድግስ እየተደገሰለት ይገኛል ። ላለፉት 30 ዓመታት በስልጣን ላይ የነበሩትና አሁንም በስልጣን ላይ ያሉት እነዚሁ ሁለት የፅንፈኛ ቡድኖች በመሆናቸው 28 ቱን ዓመት የወያኔው ትግሬ እራሱን እስከ አፍንጫው ሲያደራጅና ሲያስታጥቅ እንደቆየው ሁሉ ፣ ያለፈውን 2 ዓመት ደግሞ የኦሮሞው ኦነግ ወያኔዎችን በሚያስንቅ ፍጥነት እራሳቸውን በማደራጀትና በማስታጠቅ አማራው ላይ ከባድ ጥቃት ለማድረስ ከሰሜን በኩል ወያኔያውያን ፣ ከደቡብ በኩል ኦነጋውያን ፤ ከምዕራብ ደግሞ ባዕድ የሆነ የሱዳን (ድርቡሽን) በማስጠጋት ከበባውን እያጣደፉት ይገኛሉ ።

ገጣሚው እንዳለው ፡-

*ያንተ ልጅ ሲበላ ፣ የኔ ልጅ ያለቅሳል*
*ያንተ ቤት ተከድኖ ፣ የኔ ቤት ያፈሳል*
*ያንተ መሬት ታርሶ ፣ የኔ ዳዋ ለብሷል*
*ወይ ያንተ ፣ ወይ የኔ ፣ ያንዳችን ቀን ደርሷል*
*ጊዜ መሀንዲስ ነው ፣ ይሰራል ያፈርሳል ።*

እንዳለው ሁሉ ፣ ያንዳችን ቀን መድረሱ አጠያያቂ አይሆንም ።

በልብ ወለድ ትርክት ፣ በቂምና ጥላቻ ነቀዝ ተበልቶ ፣ ከአንድነት ይልቅ ልዩነት ፣ ከመተሳሰብ ይልቅ መተራረድን መርጦ ፣ ሳይደርሱበት ደርሶ ፣ ቀን አንስቶኛልና በአሸናፊነትና በድል አድራጊነት እወጣለሁ ብሎ ፣ በዕብሪትና በጥጋብ ተወጥሮ የሰበቁት ጦር ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ለሚያምን የጎልያድን ታሪክ ይመልከት ፣ አሊያም የቅርቡን የጣሊያንና የእምዬ ሚኒሊክን ታሪክ አገላብጦ ቢመለከት ውጤት የተገላቢጦሽ ሊሆን እንደሚችል ይገነዘባል ብለን እናምናለን ። ደመወዝ እየበላ ፣ ልጁን ለማሳደግና ቤቱን ለመደጎም ሲል ብቻ ከሚሰለፍ ሰራዊትና ፣ ለማንነቱንና ለክብሩ ፣ ለሉአላዊነቱና ርስቱን ለመከላከል ከሚወጣ ፣ ደመወዝ የለሽ አርሶ አደር ጦር ፣ ማን እስከመጨረሻ የደም ጠብታ ሊታገል እንደሚችልና በድል አድራጊነት ጉሮ ወሸባዬ እንደሚል ፣ ታሪክን ማገላበጥ እንጂ ጠንቋይ መቀለብ አያሻም ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን አበው እንደሚተርቱት *"ሞኝን አባብ ሁለቴ ይነድፈዋል"* የሚባለው እንዳይሆን የአማራው ሕብረተሰብ ከነ ጄኔራል አሳምነው ጽጌና ከነ ዶ/ር አምባቸው ግድያና ፣ የአማራውን ልዩ ኃይልና ሚሊሺያ የተቀነባበረ የደባ ብተና ትልቅ ትምህርት መውሰድ ግድ ይላል ።

በሐገር ቤትም ሆነ በዲያስፖራ የሚገኘው የአማራ ተወላጅ ፣ እንዲሁም የሌላ ብሄር ተወላጅ የሆነና ኢትዮጵያን የሚወድ ፣ ኢትዮጵያ እንደ ሐገር በአንድነቷና በሉአላዊነቷ ፀንታ እንድትኖር ፅኑ ምኞትና ፍላጎት ያለው ሁሉ ፣ አሁን በአማራው ላይ እያንዣበበ ላለው አደጋ አለምንም ቅድመ ሁኔታና ማወላወል ለአማራው ማሕበረሰብ አጋርነቱን ሊያሳይ ግድ ይላል ። *"ሞኝ ልጅ ፣ ለአባቱ ተዝካር ማውጫ ፣ በታረደ በሬ ፊኛ ይጫወታል"* የሚሉትን ያባቶች ዘዬያዊ አነጋገር ማስታወስ ብልህነት ነው ። ነገ ወደ ሌላው ሊዛመት እንደማይችል ምንም ማረጋገጫ ስለማይኖር *"ሳይቃጠል በቅጠል"* እንዲሉ ይህን አርቆ አስተዋይነት የጎደለውን አካሄድ ተባብሮ ማምከን የአማራው ግዴታ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ሁሉ ግዴታ መሆኑን መገንዘብ ያሻል ።

ለማጠቃለል ፣ በተከታታይ በአማራው ማሕበረሰብ ላይ እየመጣ ያለውን አደጋ ባለኝ ትንሽ ግንዛቤም ቢሆን ለማሳሰብና ለማስጠንቀቅ ሙከራ ከማድረግ አልተቆጠብኩም ፣ ብዙዎች በሌላ ነገር ላይ የምናገር ሊመስላቸውም ይችል ይሆናል ፣ ጉዳዩ ግን ያፈጠጠ ፣ ያገጠጠ ሃቅ ስለሆነ ከመወትወት ወደኋላ አልልም ይልቁንም *"ከብልህ የሚገኝ ሞኝነት ፣ ተራራ ያክላል"* እንዳይሆን ስጋቴ ከፍ ያለ ነው ። ስለሆነም *"ሞኝ ሲናገር ፣ ብልህ ያዳምጣል"*ና የኔ ስጋት የሞኝ ለቅሶ ሳይሆን አንባቢያን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ምልከታዬን አፅንዖት ሰጥታችሁ መደረግ ያለበትን ሳይረፍድ ሁሉን በጊዜው ታደርጉ ዘንድ አሳስባለሁ ።

ታዛቢው

April 2, 2020